# ዘጠነኛ ትምህርት ከየካቲት 18 — 24 Feb 25— Mar 3

## መንፈስ ቅዱስና ቤተ ክርስቲያን

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ኤፌ. 1:22-23፣ 1ቆሮ. 12:13፣ ሮሜ 6:3-7፣ ሐዋ. 17:11፣ ኤፌ. 4:5-6፣ ሐዋ. 2:4- 11.

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡- "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ። በተጠራችሁ ጊዜ ወደ አንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ ሁሉ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ" (ኤፌ. 4:3-5)።**

አንዳንዴ መንፈስ ቅዱስ በግለሰብ ደረጃና በግለሰብ ደረጃ ባሉ አማኞች ሕይወት ብቻ እንደሚሠራ አድርገን እናስባለን። ነገር ግን ይህ በግለሰብ ደረጃ የሚሠራ ሥራ የማኅበረሰብ መንፈሳዊነት መሰረት እንደ መሆኑ ውሎ አድሮ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መቋቋም ኃላፊነቱን ይወስዳል።

ቤተ ክርስቲያን ህልውናዋ ተጠብቆ እድገት ማግኘት የቻለችው የተለያዩ የወንጌል ስርጭቶችንና የወንጌላዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረጋችን ነው የሚለው አስተሳሰብ በተደጋጋሚ ይፈትነናል። እርግጥ ነው እግዚአብሔር የእኛ አገልግሎት የታከለበትን ለቤተ ክርስቲያን ያለውን አስደናቂ ዕቅድ ለመፈጸም ይፈልጋል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ያለችው በእኛ ብቃት ያለው አደረጃጀትና ውጤታማ (አስፈላጊ ቢሆኑም) አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ያለችው እግዚአብሔር እስከ ዛሬ ባደረገው ነገርና ይህንኑ ሥራውን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መሥራቱን የሚቀጥል በመሆኑ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል የእምነቱ መሰረት አድርጎ የሚቀበለውን መንፈሳዊ ማኅበረሰብና ኅብረት የሚፈጥረው መንፈስ ቅዱስ ነው። ያው መንፈስ--በልብ ውስጥ መነሳሳትን ለማምጣትና እምነት ነክ ለሆኑ ጉዳዮችና አተገባበራቸው ሥልጣን አለው። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጽፉ በልባቸው ውስጥ መነሳሳትን የፈጠረው መንፈስ ቅዱስ፤ የቤተ ክርስቲያን ሥነ መለኮታዊ ኅብረት መሰረት ነው። ቤተ ክርስቲያን ያለ መንፈስ ሥራ ህልውና ሊኖራትም ሆነ ተልዕኮዋን ለማሳካት መቀጠል አትችልም።

*እሑድ የካቲት 19* *Feb 26*

### መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት እንድንፈጥር ያስችለናል

መንፈስ ቅዱስ በተለያዩ መንገዶች ከእኛ ጋር አንድነት ይፈጥራል። መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያውኑ ከክርስቶስ ጋር ባያስተሳስረን እንደ ቤተ ክርስቲያን ህልውና ባልኖረን ነበር። ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን

ራስ ነው (ኤፌ. 1:22-23፣ 5:23)። እኛ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከራሱ ከክርስቶስ ጋር በብርቱ ኃይል ተሳስረናል። በጌታ ያለን ሁሉ ከእርሱ የሚመጣ እንደመሆኑ ከክርስቶስ ጋር አንድነት መፍጠር የሁሉም ዓይነት የደኅንነት በረከቶች መሰረት ነው። የክርስቶስ ወንድና ሴቶች ልጆች ሆነን መቆጠራችን፣ የጽድቅ ባለቤቶች መሆናችን፣ ቅድስና ማግኘታችን፣ በኃጢአት ላይ አሸናፊ ሕይወት መኖራችንና በስተ መጨረሻ መክበራችን--እነዚህን ሁሉ የተቀበልነው ከክርስቶስ ጋር ባለን ኅብረት ነው። ስለዚህ እርሱ የአጠቃላዩ ተሞክሮአችን የክርስትና ሕይወት መሰረት ሊሆን የግድ ነው።

**እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ኤፌ. 2:18፣ 20-22፣ 1ጴጥ. 2:6, 7። ጥቅሶቹ ለቤተ ክርስቲያን መፈጠር የክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምንድን ነበር ይሉናል?**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

ወደ አብ የምንደርስበት መንገድ እነሆ በመንፈስ አማካይነት ተቀይሶልናል። የሱስ--ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መሰረት የተጣለበትና የታነጸበት የደኅንነታችን መሰረት ዐለት ነው።

በግለሰብ ደረጃ የሚሠራው የመንፈስ ሥራ በመቀጠል ወደ ማኅበረሰብ አቀፍ እምነትነት ይሸጋገራል--ወደ ቤተ ክርስቲያንነት። በክርስቶስ የሱስ ላይ ብቻ በሚኖረን እምነት ደኅንነትን ስንለማመድና በእግዚአብሔር ፍቅር ስንነካ ጣፋጭ የሆነውን "የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት" (2ቆሮ. 13:14) በቤተ ክርስቲያን እናገኛለን። እያንዳንዱ አማኝ በየግሉ "በመንፈሱ" (ኤፌ. 2:22) በአዲሱ መንፈሳዊ ቤት ይገነባል። እንደ ክርስቶስ ተከታይነታችን "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ" (ኤፌ. 4:3) አጥብቀን ልንተጋ ይገባል። በማንኛውም ጽናታችንን በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ሳንደራደርና አቋማችንን ሳንቀይር ከአማኞች ጋር ኅብረት የምንፈጥርበትን አንድነት መሻት ከእኛ ይጠበቃል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ቆለ. 3:12-14። በጥቅሱ የቀረቡትን ባህሪያት እንዴት በአርአያነት ወስደው ለቤተ ክርስቲያንዎ ማዋል ይችላሉ? ባህሪያቱ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት መሰረታዊ የሆኑት ለምንድን ነው?

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

*ሰኞ የካቲት 20* *Feb 27*

## መንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ከእኛ ጋር ኅብረት ይፈጥራል

በ1ቆሮ. 12:13 እንደ ቀረበው--ጥምቀት ከክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንዴት ያስተሳስረናል?

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

ከአማኞች ጋር አንድ አካል አድርጎ የሚያስተሳስረን መንፈስ ቅዱስ ነው። ወደ ክርስቶስ መንፈሳዊ መንግሥት የምንገባው በጥምቀት አማካይነት ነው። በጥምቀት የአንድ ቤተ ክርስቲያን አካል ሆነናል። ስለዚህ ጥምቀት የራሱ የተለየ ማኅረሰባዊ ገጽታና አስፈላጊ ማኅበረሰባዊ አንደምታዎች አሉት። የክርስቶስ

ተከታዮች እንደ መሆናችን ከሌሎች ተነጥለን በራሳችን መኖር አንችልም፡፡ የሌሎችን ድጋፍ፣ ማበረታታትና እርዳታ ልናገኝ ይገባል፡፡ መለኮታዊውን ተልዕኮም እንዲሁ ብቻችንን ከግብ ማድረስ አንችልም፡፡ እግዚአብሔር ለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያንን የፈጠረው፡፡ ክርስቶስን መከተል ማለት ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ፈጥሮ እርሱን መከተል ነው፡፡ ስለዚህ ጥምቀትና ቤተ ክርስቲያን ለእነርሱ በጉልህ የሚታይ አካል አላቸው፡፡

*ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- ሮሜ 6፡3-7፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ተምሳሌትነቱ ምንድን ነው?*

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በጥምቀት በውሃው መቃብር ሙሉ ለሙሉ በመስጠም ከየሱስ ክርስቶስ ጋር መቀበር--ከዚያም ከአዳኛችንና ከጌታችን ከየሱስ ጋር ኅብረት በሚፈጥር አዲስ ሕይወት መነሳት--የቀድሞውን አሮጌ ሕይወት መስቀልና ክርስቶስን በሰዎች ፊት እንደ ግል አዳኛችን አድርገን መቀበላችንን ያመለክታል፡፡

"ጥምቀት ዓለምን መካዳችንን የምናሳይበት እጅግ የተከበረ ሥርዓት ነው፡፡ የክርስቶስ ሥራ ለኃጢአተኛው በመቆጠሩ እኔነትን ማዕከል አድርጎ የነበረው ኃጢአተኛ ህይወት ከዚህ በኂላ ሙት ይሆናል፡፡ ውሃው እጩ ተጠማቂውን ሙሉ ለሙሉ ሲሸፍነው በእርሱና በመላው ዩኒቨርስ ፊት የጋራ ቃል ኪዳን ይጸናል፡፡ ተጠማቂው በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ወደ ውሃው መቃብር ይወርዳል፣ በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር ይቀበራል፣ በመጨረሻም ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ በሚኖርበት አዲስ ሕይወት ሊመላለስ ከውሃው ይወጣል፡፡"–Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 6, p. 1074.

ጥምቀት በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ስር ለመመላለስ ያለንን ምኞት የምንገልጽበት አዎንታዊ እመርታ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ጥምቀት የድሮው ሕይወት የተሰቀለበት፣ የአዲስ ልደት ወይም መለወጥ ማሳያና የእውነተኛ ንስሐ ምልክት ነው፡፡ በተጨማሪ ጥምቀት የጋራ ኪዳን ግዴታዎችንም ያካተተ ነው፡፡ አማኙ ለእግዚአብሔርና ለትእዛዛቱ ታማኝ ለመሆን ቃል የሚገባበት--በአንጻሩ አማኙ ለሚያሻው ማንኛውም እርዳታ በእግዚአብሔር ላይ ሊተማመን እንደሚችል ከእግዚአብሔር ዋስትና የሚያገኝበት ነው፡፡

*ያመኑ የሚፈጽሙትን የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ለመፈጸም ውሳኔ ላይ ደርሰዋል? ውሳኔ ላይ ካልደረሱ-- በጥምቀት ክርስቶስን እንዳይቀበሉ እያስተጓጎሎት ያለ ነገር ምንድን ነው? በውሃ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ጠልቀው የተጠመቁ ከሆነ የጥምቀት ኪዳንዎ ከየሱስ ጋር በሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉዞዎ ላይ ምን ዓይነት አዎንታዊ ተጽእኖ አምጥቶአል?*

*ማክሰኞ      የካቲት 21                                                                 Feb 28*

## *መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል ከቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ይፈጥራል*

*እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ሐዋ. 17፡11፣ ዮሐ. 5፡39፣ 46- 47፣ 8፡31- 32፡፡ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መለያ ምልክት ምንድን ነው? እኛን ወደ ክርስቶስ ለማመላከትና እርሱን በታማኝነት እንድንከተለው በመርዳቱ ረገድ መጽሐፍ ቅዱስ ወደር የማይገኝት ፍጹም ቃል የሆነው ለምንድን ነው?*

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

መንፈስ ቅዱስ እኛን ከክርስቶስ ጋር የሚያገናኝበት ቀዳሚው መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የሱስንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት ያለው ምንጭ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና መልእክቱን በአእምሮ መያዝአስፈላጊ የሆነው ለዚህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊውን እውነትና ስህተት ለመለየት ሥልጣን ያለው ምንጭ ነው። ጳውሎስ የቤርያ ሰዎች (ሐዋ. 17፡11) ስለነበራቸው አስተዋይ አእምሮ አመስግኗቸዋል። ምክንያቱም እነዚህ ሕዝቦች የሰሙት መልእክት እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት ያጠኑና ይመረምሩ ስለነበር ነው።

በግልም ይሁን እንደ ቤተ ክርስቲያን የቱንም ዓይነት ተጽእኖ ሊያሳድርብን የሚችል ማንኛውም ተሐድሶ ወይም መንፈሳዊ መነቃቃት--መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረተ ሊሆን የግድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እምነታችን የተገነባበት መሰረት ነው። በየሱስና በጽሑፍ በቀረበልን ሕያው ቃሉ ላይ የሚኖረን ፍቅር ከእርሱ ጋር በአንድ ያስተሳስረናል።

የሱስ በዮሐ. 17፡17-21 የክርስትና ዓይነተኛ መለያ ስለሆነው ኅብረት ይናገራል። በዮሐ. 17፡17 እንደ ተመለከተው የዚህ ኅብረት መሰረቱ ምንድን ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው (ዮሐ.1 7፡17፣ መዝ. 119፡160)። የቤተ ክርስቲያን ኅብረት መንፈስ ቅዱስ በሕያው ቃሉ አማካይነት የሚሠራው ሥራ ውጤት ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ ጥርጣሬ፣ ትችት፣ ከተቀመጠልን ገደብ አልፈን እንድንሄድ ወይም ከዚያ በታች እንድወርድ ፈጽሞ አይመራንም። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስ ላለው መለኮታዊ ሥልጣን አድናቆትና ምስጋናን እንድናቀርብ ይመራና። መንፈስ ቅዱስ ሕያው ከሆነው አምላካዊ ቃል እንድናፈገፍግ አያደርገንም። በተቃራኒው ሳናሰልስ በማስተዋልና በፈቃደኝነት ከመልእክቱ ጋር ትስስር እንድንፈጥር ያስችለናል። መጽሐፍ ቅዱስ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው የማንኛውም ዓይነት ሥነ መለኮታዊ ኅብረት መሰረት ምንጩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን እግዚአብሔር ለእኛ እንደ ሰጠን አምላካዊ ቃል በመቀበል ፋንታ አሳንሰን የምንመለከተው ከሆነ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ይጠፋል።

በየቀኑ ቃሉን ለማጥናት ምን ያህል ጊዜ ይወስዳሉ? ከሁሉ በላይ--ራስዎን ለአምላካዊው ቃል አስተምህሮ መስጠትን መማር የሚችሉት እንዴት ነው?

### *ረቡዕ የካቲት 22* *Mar 1*

### መንፈስ ቅዱስ በእምነትና በኃይማኖታዊ አስተምህሮ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ይፈጥራል

**"አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፤ ከሁሉም በላይ የሆነ፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉ የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ" (ኤፌ. 4፡5, 6)። ጳውሎስ ስለ ኅብረት ምን እያለን ነው? ይህ ኅብረት ከወዴት ይመጣል ይለናል?**

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ በመሆን ብቻ የእምነትና የኃይማኖት አስተምህሮ ኅብረት መምጣት ይችላል። ትናንት፣ ዛሬ፣ ነገም ሆነ ለዘላለም ያው የሆነው ጌታ ከእያንዳንዱ አማኝ ጋር መንፈሳዊ ትስስር ይፈጥራል። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ገቢራዊ የሚሆነው ያው አዲስ ልደት፣ መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠን

ኃይል ለእግዚአብሔር ቃል የሚኖረን ያው ታዛዥነት--መላውን ሰብዓዊ ዘር ከነባህል ልዩነቱ ወደ ተሻለ የእምነት አንድነትና ተግባር ይመራል፡፡

ራሳችንን ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ እንድናደርግና ከእያንዳንዱ ሰው ጋር ሰላም ለመፍጠር ማድረግ የምንችለውን ሁሉ እንድናደርግ ተጠርተናል (ሮሜ 12፡18)፡፡ ከዚህ ውጪ የኃይማኖታዊ አስተምህሮም ሆነ የዓላማ አንድነት ማምጣት አንችልም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት በአብዛኛው እኛ ሠርተን የምናመጣው ነገር ሳይሆን ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ በግልና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተባብሮ የሚሠራው የእርሱ ስጦታ ነው፡፡

የዚህ ኅብረት ሥነ መለኮታዊ መሰረት የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ለመንፈስ ቅዱስ የሚደረግ አምላካዊውን ቃል መሰረት ያላደረገ ማንኛውም ዓይነት ተማጽኖ በኃይማኖታዊ አስተምህሮና አተገባበር ላይ የጥርጣሬ ዘር እንዲዘራ መንስኤ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ መንፈስ ቅዱስን አግልሎ በአምላካዊው ቃል ላይ የሚቀርብ ማንኛውም ዓይነት ልመና ቃሉን ደረቅና መካን ያደርገዋል፡፡ አንድ ጌታ ብቻ በመኖሩ ምክንያት--ወደ አንድ ጥምቀት የሚመራ አንድ ብቻ እምነት አለ፡፡ በደስታ የተሞላውን ታማኝነት ለእግዚአብሔር ቃል ስናሳይ ብቻ በቤተ ክርስቲያናችን ኅብረት ሰፍኖ ማየት እንችላን፡፡ በእምነታችንና በኃይማኖታዊ አስተምህሮአችን ላይ ኅብረት ከሌለን የተሰጠንን ተልዕኮ ማስፈጸም የሚችል አንድነት አይኖረንም፡፡

"አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለን፡፡ የክርስቶስ ወንጌል ወደ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ ብሔሮች፣ ቋንቋዎችና ሕዝቦች መድረስ ይኖርበታል፡፡ የወንጌል ኃይል እንደ አንድ የወንድሞች ኅብረት ሊያስተሳስረን ይገባል፡፡ ጸባያችንን በማጎልበቱ ረገድ ልንመስለው የሚገባ አንድ ብቻ ይኸውም--የክርስቶስ ምሳሌ አለን፡፡ ከእርሱ ጋር ፍጹም ስምምነት ስንፈጥር ሰዎች የሱስ ክርስቶስን መምሰል ይጀምራሉ፣ በአንድ ሐሳብና በአንድ ልብ ይሆናሉ፣ ንግግራቸው ተመሳሳይና--እግዚአብሔርን በአንድ አንደበት የሚያወድሱ ይሆናሉ፡፡"–Ellen G. White, Our High Calling, p. 171.

**የሌሎች ጉዳይም ሆነ ሌሎች የሚያደርጉት ነገር ሳያሳስቦት፡ አስገራሚው አምላካዊ ኅብረት የታለመለትን ግብ እንዲመታ የበኩሌን ምን ማድረግ እችላለሁ? ብለው ራስዎን ይጠይቁ፡፡**

*ሐሙስ የካቲት 23* *Mar 2*

## *መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን በተልዕኮና በአገልግሎት አንድ ያደርጋል*

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- ሐዋ. 2፡4-11፣ 16-21፡፡ በአዲስ ኪዳን አማኞች ላይ ፈስሶ የነበረው መንፈስ ቅዱስ ያስከተለው ውጤት ምን ነበር?**

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ካላቸው ምዕመኖች ይልቅ በአንድ ልብ ሆነው በሚያመልኩት አነስተኛ ቁጥር ባላቸው አባላት ታላቅ ሥራ መሥራት ይችላል፡፡ ሆኖም እኛ ሁላችን ሕይወታችንን፣ ጉልበታችንን፣ መክሊቶቻችንንና ገንዘባችንን ለእርሱ ስናውል እግዚአብሔር ከዚያ የላቁትን ነገሮች ማድረግ ይችላል፡፡

የአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን አባላት በሕይወታቸውና በተልዕኮአቸው ኅብረት ፋና ወጊዋን ቤተ ክርስቲያን አሳደጓት፡፡ እነዚያ እፍኝ የማይሞሉ ድፍረተ ቢስና ዐይን አፋር አባላት--ውጤታማውን ዘዴ ተጠቅመው በአንዴ ወደ ተለያዩ ባህሎችና ቋንቋዎች በመድረስ ወደ ኃያል ሰራዊትነት ለመለወጥ ቻሉ፡፡ አማኞች በአንድነት ሆነው "የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ" (ሐዋ. 2፡11) ያውጁ ነበር፡፡ በአዲስ ኪዳን ዘመን በብርታት

የሠራው ያው አምላክ ከዳግም ምጽአቱ አስቀድሞ--በምድር ታሪክ መደምደሚያ ላይም እንዲሁ በተመሳሳይ ኃይል ይሠራል።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ሐዋ. 2፡42-47። የአዲስ ኪዳን አማኞች በሌሎች በምን ዓይነት ተግባራት ኅብረት ፈጥረው ነበር?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የጴንጤቆስጤው ተልዕኮ እንቅስቃሴ የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን በአንድ ያስተሳሰሩ ተጨማሪ ሌሎች አያሌ ጉዳዮችንም ያካተተ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስን ሁል ጊዜ በኅብረት የሚያጠኑና ራሳቸውን ለሐዋርያት ትምህርት ያዋሉ ነበሩ (ሐዋ. 2፡42)። በኅብረት ሆነው ከአምላካዊው ቃል ይቆርሱ (አምልኮ ያደርጉ) ነበር (ሐዋ. 2፡42)። እግዚአብሔርን በማመስገንና (ሐዋ. 2፡47) በጸሎት ይተጉ ነበር (ሐዋ. 2፡42)። የነበራቸውን ለሌሎች በነጻ እያካፈሉና ያላቸውን በጋራ እየተጠቀሙ በችግር የነበሩ ወገኖችን በኅብረት ያገለግሉ ነበር (ሐዋ. 2፡44-45)። በአንድነት የሚደረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ኅብረት መልካሙን የምስራች ለሌሎች የማካፈል ምኞት እንዲቀሰቀስ የማድረግና ሌሎችን በተጨባጭ የመርዳት ውጤት ያስገኛል። መንፈስ ቅዱስ በዙሪያችን የሚገኙትን በችግር ያሉ ወገኖች መመልከት እንድንችል ዐይኖቻችንን ይከፍታል።

የቤተ ክርስቲያናችሁን ኅብረት ለማግለጥ የሚያስችሉ ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ መካሄድ ይኖርባቸዋል? አሁን እየተተገበረ ካለው በበለጠ ምን ሊሠራ ይገባል?

*ዐርብ      የካቲት 24                                                                                    Mar 3*

## ተጨማሪ ሃሳብ፡-

"በዚህ ሥራ ላይ ሁላችንም ልንሰማራ ይገባል። በይዘቱ ከወትሮው ለየት ያለ አስደሳች ጊዜ ከዛሬ ነገ ይመጣል እያሉ ከመኖር--ለነፍሳት ደኅንነት ዛሬ እጃችን ላይ ያሉትን ዕድሎች በብልሃት ልናበለጽጋቸውና መደረግ የሚኖርባቸውን ልናደርግ ይገባል። ጌታ ከሰዎች ሰውሮ በራሱ ኃይል የመደባቸውን ጊዜያቶችና ወቅቶች በራሳችን ግምትና ንድፈ ሀሳብ የአእምሮአችንን ኃይል ከምናዳክም ይልቅ--ራሳችንን ተቆጣጥረን ለመንፈስ ቅዱስ ልናስገዛ፣ የየዕለቱን ግዴታችንን በአግባቡ ልንወጣና እውነትን አጥተው እየጠፉ ላሉ ነፍሳት በሰብዓዊው አመለካከት ያልጎደፈውን የሕይወት እንጀራ ልንቆርስ ይገባል።"–Ellen G. White, Selected Messages, book 1, p. 186.

"እያንዳንዱ ግለሰብ የትኩረት እምብርት ለመሆን ብርቱ ፍልሚያ እያደረገ እንደ መሆኑ--እግዚአብሔር ለሕዝቡ እስከሚሠራ በስሩ ውሎ ማደር ለእያንዳንዱ ነፍስ ብቸኛው መጠበቂያ መንገድ መሆኑን አይመለከቱም። ሰብዓዊን ልብ የሚለውጠው አምላካዊ ጸጋ እስከ አሁን በሚገባ ወዳልተስተዋለው ኅብረት ይመራናል። ከክርስቶስ ጋር ትስስር የፈጠሩ ሁሉ እርስ በርሳቸውም ስምሙ ይሆናሉ። መንፈስ ቅዱስ ኅብረት ይፈጥራል።"–Ellen G. White, Selected Messages, book 3, pp. 20, 21.

## የመወያያ ጥያቄዎች

- ኤለን ኋይት “እያንዳንዱ ግለሰብ የትኩረት እምብርት ለመሆን ብርቱ ፍልሚያ እያደረገ” ይገኛል ስትል ምን ማለቷ ነው? ይሄ ነገር የሁላችንም ተፈጥአዊ ዝንባሌ የሆነው ለምንድን ነው? ይህን ዝንባሌ በየራሳችን ሕይወት ለመፋለም ምን ማድረግ እንችላለን? (ፊልጵ. 2:3, 4)
- አንዳንዶች በትክክል አንድ ሊያደርገን የሚችለው አገልግሎት እንጂ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ አይደለም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ሰዎችን የመከፋፈል አዝማሚያ ስላለው በግልጽ የሚታይ ሆኖ ሊቀርብ አይገባም--በሚል እሳቤ፡፡ ታዲያ በኃይማኖታዊ አስተምህሮ ላይ መከፋፈል ካለ በተልዕኮና በአገልግሎት ዙሪያ አንድነት መኖር ያልቻለው ለምንድን ነው? በጋራ የተወሰደው እምነት አንድነት ለመፍጠርና ለውጤታማ ተልዕኮ ኃይል መሆን ያልቻለው ለምንድን ነው?
- በተመሳሳይ--ለሥነ መለኮታዊ ልዩነቶችስ ምን ያህል መቻቻያ መንገዶች አሉ? ጥቂት ሰዎች ብቻ እውነትን እንዳለ ያስተውላሉ፡፡ በመሃላችን ያሉ ጥቂት ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው እንደ ቤተ ክርስቲያን በአንድነት መቆም የምንችለው እንዴት ነው? የእርስዎ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በመሀላቸው ያሉ ልዩነቶችን በማስተዋል ኅብረታቸውን ግን የተጠበቀ ለማድረግ የሚሠሩት እንዴት ነው?
- መጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት ማምጫ መሣሪያ መሆን የሚችለው እንዴት ነው? በወንጌል ተልዕኮም ሆነ በእምነት--ኅብረታችን የተጠበቀ መሆን እንዲችል የእግዚአብሔርን ቃል ስናጠና ምን ዓይነት አቋም ልንይዝ ይገባል፡፡